# ምክር፦ ለኦሮሞ ጠባብ (ፖለቲከኞች፣ አክቲቪስቶች፣ጸሃፊዮች፣ ጋዜጠኞች፣ ቄሮች፣ሊሂቃን ወዘተርፈ)

ታጠቅ ዙርጋ ፤

***27 December 2019***

ካልተሳሳትኩ የትኛውም አገር ማኅበረሰብ አገሩና ቤቱን የሚጎበኝ እንግዳ ከታላቅ አክብሮትና ስብዕና ጋር ያስተናግዳል። በተመሳሳይ አገርና ሕዝብን የማስተዳደር ዕድል የገጠመው በሳልና ሥልጡን ቤተሰብ ለሚያስተዳድሩት ማኅበርሰብ በጣም ታዛዥና ትሁት ይሆናሉ።

ለዚህ ማስረጃ እኔ ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ፦

< በሃይማኖት ተቋማት የሚያገለግሉ ማለት የቤተክርቲያን ቄስ/ሶች እና የመስጊድ ሼክ/ዎች ቤተሰቦች

< በአካባቢዩ ማኅበረሰብ መካከል ቅራኔና ሌላች ችግር ሲፈጠር የሚፈቱ እውቅ ሽማግሌዎች ቤተሰቦች

< የዕድር ኮሚቴ አባላት ቤተሰቦች

< የመምህራን ቤተሰቦች ወዘተርፈ ለማኅበረሰቡ በጣም ትሁትና ታዛዥ ናቸው።

አባቶቻቸውን፣ወንድሞቻቸውን፣ አጎቶቻቸውን፣ጎሳዎቻቸውን ወዘተ..የአካባቢያቸውን ሕዝብ አገልጋይ ለመሆን በመብቃታቸው እንደመታደል ይቆጥሩታል ።ማኅበረሰቡን የማገልገል ዕድልና ሃላፊነት በእነሱ ቤተሰብ ጫንቃ እንደወደቀ ይረዳሉ/ይገነዘባሉ። ስለሆነም ወደ መሬት ዝቅ ብለው ማኅበረሰቡን ሲያገለግሉ ይታያሉ።

በዚህ በምንኖርበት ዓለም ሰዎች ከሚመኙዋቸው ትላልቅ ነገሮች አንዱ የፖለቲካ ሥልጣን ነው። በመሆኑም የኦሮሞ ወገኖቻችን የአገራችንን ታሪካዊ አጋጣሚና ነባራዊ ሁኔታዎችን በመጠቀም ለረዥም ዓመታት ሲመኙት የነበረውን የአገራችንን በትረመንግሥት በእነሱ ሃይል <power> ወድቋል ።

ሀ) ከኦሮሞ አባት አብራክ የወጡ አብይ አህመድ የአገራችን ጠ/ሚ በመሆን የብሄራችን ቤተመንግሥት ገብቷል ። ለእኔ ቤተመንግሥት ሳይሆን ቤተጥፋት ነው።

ለ) 70% ያህሉን ቁልፍ ቁልፍ የ(የመከላኪያ፣ የፖሊስ፣የጸጥታ፣የመገናኛ፣የትራንስፖርት፣የጤና፣የባንክ ፣ የከተማዎች ወዘተርፈ ተቋማትና ሌሎች የአሰዳደር ዘርፎች ሥልጣን በኦሮሞች መያዙን በተለያዩ ጋዜጠኞችና አክቲቪስቶች ተነግሮዋል

ሐ) በርዥም ዘመን ሉዓላዊ፣ሕዝባዊና ፖለቲካዊ ታሪካችን ውስጥ ያልተደረገ የሬቻ በዓል በዚህ ወቅት በአገራችን መናኽርያ በአዲስ አበባ መከበር

መ) ደርጎች አብዮት አደባባይ በሚሉት ኢትዮ- ሕዝባውያን መስቀል አደባባይ ብለን በምንጠራው አጠገብ ካለው ትልቅ የኦሮሞ ባህል ተቋም በተጨማሪ እና ከሌሎች ከሰማኒያ በላይ ከሚሆኑ ብሄር ብሄረሰብች በተለየ ለኦሮም ባህልና ልማት ተቋም የሚውል ግዙፍ ሕንጻ ለመሥራት ብዙ ብሊየን ብር መመደቡን በሚዲያ ከተገለጸ ሰንብቷል

ሠ) የኦሮሞ አክራሪ (ፖለቲከኞች፣ቄሮች፣አነጎች፣አክቲቢስቶች፣ጋዜጠኞች) ወዘተርፈ -እነዚያ በማለት የሚጠሏቸውን በፈለጉት ግዜና ሰዓት ከቀያቸው ማፈናቀል ፣ ገለውና አስገድለው ያለመከሰስና ያለመ ቀጣት መብት ማግኘት

ረ) ኦርሞ ነዋሪዮች ይበዙበታል በተባሉ አካባቢዮች በሚሰሩ የመኖሪያና የንግድ ቤቶች በኦሮሞች ብቻ መያዝ

ሰ) ለኦሮሞች መብትና ጥቅም ብቻ የሚሚገት፣ የፈለገውና የሚወደውን የሚቀሰቅስና ፕሮፓጋንድ የሚነዛ ወዘተርፈ ግዙፍ የሚዲያ ተቋም ባለቤት መሆን መቻል

ሸ) የአዲስ አበባ ባለቤትነት የመጠየቅ የሞራል ድፍረት ማግኘት

ቀ) ሥልጣን ወይም ሽሞት ለየአንዳንዱ ኦሮሞ ቤት ካልገባ ካላሉ በስተቀር ፤ የኦሮሞ ወንድሞቻችን የወቅቱን የኢትዮጵያ ሃያል ብሄር ለመሆናቸው ከሚያሳዩ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ስለሆነም የሚከተሉትን 'ነቅዕ ወይም ምጥቅ' ምክሬን በተግባር እንዲያውሉ አሳስባቸዋለሁ

ከላይ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ እንደጠቆምኩት እናንተም እንደ አንድ ምኞቱ የተሳካለት ሰው ወይም ቡድን ፡-

- እጅግ በጣም ደስተሰኛ ሁናችሁ ፣የደስታ ኩራት አንግባችሁ ፣ በጣም ትሁት ሁናችሁና ወደ መሬት ዝቅ ብላችሁ (as humble as down to earth) በሰለጠነ መንገድ ኢትዮጵያውያን ማገልገል ይጠበቅ ባችኋል ወይም ይኖርባችኋል

- ይህ ቤታችሁ የገባ የሥልጣን ዕድል -(ከማገጣችሁበት፣ግፍ፣ ከፋት፣ተንኮል) ወዘተርፈ ከሰራችሁበት ሥልጣን በእናንተ ላይ ሠራ እንጂ እናንተ ባገኛችሁትን ሥልጣን አልሰራችሁበትም ማለት ነው ። - በያንዳንዱ

ለግልም ሆነ ለማኅበራዊ ህይወት በምንከነውናቸው ወይም በምንሰራቸው ነገሮች ላይ አሉታዊ ወይም አውንታዊ ዋጋ እንደሚያስከፍለን ለብዙ ዎቻችን ግልጽ ይመስለኛል ።

- አገርና ሕዝብ የማስተዳደር ዕጣ ፋንታ ደርሷችሁ በአግባብና በቅጡ ካልተጠቀማችሁበት ፤ እንደ ወያኔ

ታንቅራችሁ ትተፋላችሁ፣ ተወግራችሁ ትወገዳላችሁ ። ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ ይባላልና።

ከማኅፀኗ የውጡ ልጆቿ ያዳላሉ እንጂ እናት ኢትዮጵያ አታዳላም

እናት ኢትዮጵያ ብታዳላ ኖሮ ((የብዙ ሺ ዘመን የወል ታሪካችን ለታሪክ ፀሃፊዮች ትቼ) ከ 20 ኛ መቶ ክ/ዘመን ኢጋማሽ ጀምሮ ፤

ኢትዮጵያ የእኛ አይደለችም፣ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢያችን ናት፣መሪዮቿ ጨፍጭፈውናል፣የኦሮሞ እናቶች ጡት ቆርጧል፣ትምህርት ከልክለው አደንቁርውናል ፣የሬቻ በዓል አዲስ አበባ ወስጥ እንዳና ከብር ተከልክለናል ወዘተርፈ በማለት የሚጠሏትና የሚከሷት (ፖለቲከኞች፣ሊሂቃን፣አክቲቪስቶች፣ጋዜጠኞች፣ፀሃፊዮች ወዘተርፈ) ካሉበት ብሄር፤

ለዓለም ከፍተኛ የኖብል ሽልማት አታበቃም ነበር ። ጠ/ሚኒስተር አብይ ለኖብል ሽልማት ያበቃቸው ሰማዊ/ውጫዊ ምክንያቶች በኖብል ሽልማት ኮሚቴ ቢገለጹም ወርቃዊ/ወስጠ ዌራዊ ምክንያቱ እኛ በማንረዳው በእናት ኢትዮጵያ ረቂቅ ወይም ሚስጥራዊ ኩነት ፍቃድ ሊሆን ይችላል። ማለት በእናት ኢትዮጵያ አድባር (Spirit) ታግዞ ሊሆን ይችላል።

የአውስትራሊያ ጥንታዊ አቦርጅኖች፣ የካናዳ ጥንታዊ ኢንዊቶች፣ የአሜሪካ ጥንታዊ ቀይ ሕንዶች፣ የሜክሲኮ ጥንታዊ ማያዎች፣ የዩኩዌደር <Eucader>ጥንታዊ ኢንካዎች ፣ጥንታዊ ፓፓዎች ፣ቫናዋቶች፣ የኒዘላንድ ሞሪዮች ወዘተርፈ በዚህ ያምናሉ ። እያንዳንዱ ተፈጥሮ ወይም ግኝት( መሬት፣ወንዞች፣ተራሮች፣ ዛፎች ኩሬዎች፣ ባህሮች ፣ እንስሳት ወዘተርፈ) መንፈስ <spirit> አላቸው ብለው ያምናሉ። እነዚህ መንፈሶች ስውር/ድብቅ ሃይል እንዳላቸውም ያምናሉ። መከፋታቸውም ሆነ መደሰታቸውን የሚያሳዩት በሥውር ክስተት ነው ብለው ያምናሉ። በቅድመ ክርስትናና በቅድመ እስልምና በዚህ ምድር የኖሩ ሰዎች ሁሉ ተመሳሳይ እምነት ነበራቸው። በተፈጥሮ አካባቢያቸው ማለት ***(by natural environment)*** ያምኑ ነበር።

ሁለት ሳይንትስቶች በዚህ ነጥብ ላይ ከአባቢያቸውን ማኅበረስብ ጋር በተወያዩበት መድረክ ተገኝቼ ስለነበረ ‘ሳይንስ ያልደረሰባቸው ኩነቶችና ክስተቶች ጭራሽ የለም አንልም ሲሉ ሰማኋቸው’ ። ከእነዚህ ጥንታዊ ሕዝቦችና ሳይንትስቶች

እምነት ወይም እይታ አንጻር የኢትዮጵያ *(ምድር፣ወንዞች፣ተራሮች፣አዝ እርት፣ኩሬዎች፣ዋሻዎች እንስሳት፣ አድባራት ወዘተርፈ)* ወይም መናፍስት ***<spirits>*** ከጠቅላይ ሚኒስተር አብይ ጎን ተሰልፏል ማለት ነው ።

ከእነዝህ እምነቶች አንጻር<perspective> መለስ ዜናዊ በሽታ አይደለም ዕድሜውን ያሳጠረው ። የኢትዮጵ ያ ሕዝብ እምባና የእነዚህን አድባራት ወይም መናፍስት ቁጣ ነው ሞቱን ያፋጠነው ። ምክንያቱም መለስ ዜናዊ ፦ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ጎድቷል። የኢትዮጵያ ባንድራ፣ታሪክ፣ባህል፣ቋንቋ ወዘተ..ክፉኛ ንቋል።የኢትዮጵያን አንገት በመቁረጥ ከአንገቱ የተቆረጠ ቅል አስመስሏታል። በባህር ከሌላው ዓልም እንዳትገናኝ በሩን እንድተዘጋ ቤት አድርጓታል ።ኢትዮጵያውያንን በጎሳ ቋንቋ የድንበር ችካል ተግሎ አንክሷል/አፋጅቷል። የእሱን አገዛዝ የሚጻረሩ የደፈጣ ተዋግዮች እንዳይኖሩ ወይም እንዳይጠለሉ ሰፋፊ ድኖችን በእሳት አጋይቷል። በነዚያ ደኖች የታቀፉ ፦ አራዊት፣አእዋፍት ፣እንስሳት ፣ተባያት፣ በደረታቸው የሚሳቡ ፍጥረታት ወዘተ..ከደኖቹ ጋር አብረው ጋይቷል ። በመሆኑም የእነዚህን ሁሉ መናፍስት ***<spirits>*** መከፋትና መቆጣት እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ እምባ የመለስ ዜናዊ ሞት መፋጠን ምክንያት ናቸው ። መለስና የእሱ ካድሬ የነበረው አቡን ተብዬው በሞቱ ማግሥት ከዚህ ጽሁፍ ጋር ተዛማጅነት ያለው አጭር በእንግሊዝኛ የጻፍኩት ጽሁፍ ለድረ ገጾች ልኬአለሁ ፤አባዝቼም በአካባብዬ ለኮምኒቲዬ አባላት አድዬአለሁ።

አልበርት አንስታይን ሃማኖት ባይኖር ሳይንስ አይኖርም ነበር እንዳለ ሁሉ ኤቨርሊን ሂል ታዓምር/ታዓምራዊነት(Mystcism) የሰው ልጅ የእምነት ንቃተኅሊና እድገት መሰረት ነው ይላል ።

ታዓምር/ታዓምራዊነት የዕውቀቶችና የምርምሮች ሁሉ መሠረት/መነሻ ነው።